# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 199 የካቲት 29 2004 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የተስፋ ጭላንጭል እያሳየ ያለው የትብብር መንፈስ እንዲጎለበት የበኩሉን የሚቻለውን ሁሉ ብርቱ ጥረት ያደርጋል። ግንቦት 7 የትብብር አድማሳችንን ማስፋት አለብን ብሎ ያምናል። የምንፈጥራቸው ትብብሮችም ዘላቂና አዝላቂ እንዲሆኑ ከጅምሩ ጀምሮ በጥንቃቄ ሊገነቡ ይገባል ብሎ ያምናል፤ ለዚህም የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማበርከት ዝግጁ መሆኑ በድጋሚ ያረጋግጣል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ጥምረት ለነጻነት ፍትህና ለ እኩልነት ከኦርሞ ነጻነት ግንቦት ጋር በመተባበር በ11 ከተሞች እያካሄደ ያለው ህዝባዊ ስብሰባ እንደቀጠለ ነው

በጀነራል ከማል ገልቹ የሚመራው የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ከጥምረት ለፍትህ ለነጻነትና ለእኩልነት ጋር በመተባበር በአሥራ አንድ የዩናይትድ ስቴትስ፤ የካናዳና የአውሮጳ ከተሞች እያካሄደ ያለው ስብሰባ ባለፈው ቅዳሜ ና እሁድ የካቲት በርካታ ኢትዮጵያዊያን በሚኖሩበት በካናዳይቱ አገር ካልጋሪና በዩናይትድ ስቴትስ ግዛት በአትላንታ መካሄዱን ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰው ዘገባ አመለከተ።

ቅዳሜ የካቲት 24 2004 ዓ/ም በካልጋሪ ካናዳ በተካሄደው የጋራ ስብሰባ ኦነግን በመወከል ንግግር ያደረጉት የግንባሩ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የሆኑት አቶ ተማም ባቲ ሲሆኑ ጥምረትን በመወከል ዶር አያሌው አክሎግ እንዲሁም ዝነኛው የኪነጥበብ ሰውና የፖለቲካ አክቲቪስት ታማኝ በየነ ናቸው።

እንዲሁም በማግስቱ ዕሁድ የካቲት 25 በዩናይትድ ስቴትስ አትላንታ ተመሳሳይ ስብሰባ የተደረገ ሲሆን የጥምረቱ ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፤ የኦነግ ሥራአስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ዶ/ር ኑሮ ዳዳፎና ታዋቂው ኢኮኖሚስት ዶ/ር ጌታቸው በጋሻው እንደነበሩ ለማወቅ ተችሎአል።

በካናዳና በሰሜን አሜሪካ በመካሄድ ላይ ባሉ ስብሰባዎች የኦሮሞ ነጻነት ግንባርን በመወከል ንግግር እያደረጉ ያሉት ከፍተኛ የአመራር አባላት ድርጅታቸው ኦነግ ላለፉት 40 አመታት ከየት ተነስቶ የት እንደደረሰና ለምን የፕሮግራም ተሃድሶ ለማድረግ እንዳስፈለገ በዝርዝር የገለጹ ሲሆን አዲሱ የፕሮግራም ለውጥ ይፋ ከሆነበት ያለፈው ጃንዋሪ መጀመሪያ ጀምሮ ከአገር ቤትም ሆነ ከውጪ ከሚኖረው የኦሮሞ ህብረተሰብ ከፍተኛ የሆነ ድጋፍ እየተገኘ መሆኑን ገልጸዋል።

ባለውፈው ቅዳሜና እሁድ በተደረጉ ስብሰባዎች ጥምረትን በመወከል ንግግር ያደረጉ የአመራር አባላት ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በአገራችን ላይ እያደረሰ ያለውን በደል በሰፊው በመግለጽ ወያኔ በህዝባችንና በአገራችን ላይ እየፈጸመ ያለውን ሰቆቃ ለማስቆም የጋራ ትግል አስፈላጊነት ከምንጊዜውም በላይ እየጎላ መምጣቱንና ለዚህም ደግሞ የኦነግ የፕሮግራም ማሻሻያ አድርጎ ኢትዮጵያ አገራችንን ፍትህና እኩልነት የሰፈነባት አገር ለማድረግ የሚደረገውን ትግል ለመቀላቀል መወሰን ለመላዉ ለዲሞክራቲክ ሃይሎች መልካም ዜና ሲሆን ለወያኔና የኢትዮጵያን ውድቀት ለሚመኙት ደግሞ መርዶ መሆኑን አብስረዋል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በኖርዌይ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ታላቅ የተቃውሞ ሰልፍ አካሄዱ

ባለፈው አርብ የካቲት 23 2004 ዓም በኖርዌይ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን በዋና ከተማዋ ኦስሎ ጠንካራ የተቃውሞ ሰልፍ ማካሄዳቸውን በቦታው የሚገኘው የግንቦት7 ዘጋቢ ገለጸ።

የተቃውሞ ሰልፉ አዘጋጆች እንደገለጹት የሰልፍ ዋና ዓላማ የመኖሪያ ፈቃድ የሌላቸውን ወደ ሀገራቸው በማስገደድ ለመመለስ በኖርዌይ መንግስትና በዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ መካከል የተደረገውን ስምምነት በመቃወም እንደሆነ ተገልጿል።

ቁጥራቸው ከ500-700 የሚገመት በተለያየ ዕድሜ ክልል የሚገኝ ህዝብ እንደተሳተፈበት የተዘገበው ይህ የተቃውሞ ሰልፍ ከኦስሎ ሴንተራል ስቴሽን በተለምዶ ነብሩ ከሚባለው (የነብሩ ሃውልት ካለበት) በመነሳትና የተለያዩ መፈክሮችን በማሰማት በመጀመሪያ ያመራው ወደ ኖርዌይ ፓርላማ ሲሆን ቀጥለውም ተቃዋሚ ሰልፈኞቹ ወደ ኖርዌይ ውጭ ጉዳይ ሚንስትር ቢሮ በመሄድ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ጨቋኝ እንደሆነና ዜጎችን ባመለካከታቸው ብቻ እንደሚገርፍ እንደሚያስር እንደሚያሰቃይና እንደሚገደልም በመግለጽ ተቃውሟቸውን አሰምተዋል። ሁሉም ተቃዋሚዎችና ተቺ ጋዜጠኞች በመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ መጨረሻቸው ወህኒ መውረድ ወይም ሞት እንደሆነ አጠንክረው የገለጹት ሰልፈኞች ባለፉት ዓመታት መለስ ዜናዊንና አገዛዙን ኦስሎ ከተማ ላይ በአስጨናቂ ተቃውሞ ሰልፍ አርበድብደናል አሳፍረናል ድምጽ ለሌለው ወገናችንም ድምጽ ስንሆን ኖረናል ብለዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ተቋማትና ዘርፎች በሙስና ተተብትበዋል፣ በአቅም ማነስ ተልፈስፍሰዋል፤ የፍትህ ስርዓቱም ተደርምሷል ሲል አፍቃሬ ወያኔ የሆነው ሪፖርተር ጋዜጣ አስታወቀ

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ስልጣን ላይ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ በሃገሪቱ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ፍጥነት እየተስፋፋ የመጣው ሙስና ባስከተለው የሃብት ዘረፋና ምዝበራ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ለከፋ ድህነትና የኑሮ ጉስቁልና በመዳረጋቸው በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ብሶትና ምሬት በተደጋጋሚ እየዘገበ ያለው ሪፖርተር፤ ሙስናን ለመዋጋት መሰረታዊ የሆነ ለውጥ እንደሚያስፈልግና መፍትሄው መቀባባት ሳይሆን አፍርሶ መገንባት እንደሆነ ባለፈው እሁድ ዘገባው ገለጾአል።

ከግማሽ በላይ የሆነው ህዝባችን በቀን አንድ ጊዜ እንኳ መብላት እየተሳነው ባለበት በዚህን ሰዓት ሀገሪቱ በኢኮኖሚ "እጥፍ ድርብ እያደገች ነው" በማለት የወያኔ መሪዎች የሚያሰሙት አደንቋሪ ፕሮፓጋንዳ ርካሽ የፖለቲካ ጥቅም ለማግኘት ታስቦ እንደሆነ በሁሉም ዘንድ በመታወቁ ሪፖርተርን የመሰለ የስርዓቱ አቀንቃኞች ሳይቀሩ በወያኔ ጸረ አገር ፖሊሲ ምክንያት እየተባባሰ የመጣውን ችግር መደበቅ ከማይችሉበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል።

ለሃብት ዘረፋና ምዝበራ እንዲመቸው ብቃትና ችሎታ የሌላቸውን የፖለቲካ ታማኞች ከላይ ከማዕከላዊ መንግሥት የሥልጣን እርከን እስከ ታች ወረዳና ቀበሌ የኮለኮለው ዘረኛው መለስ ዜናዊ፡ የሙስና እሜቤት የተባለቺውን ባለቤቱን አዘብ መስፍንና እራሱና ነጻ በሚያስመስል ውንጀላ በቅርቡ ለፓርላማ ባደረገው ንግግር በሙስና ያሰማራቸውን ጭፍሮቹን "የመንግስት ሌቦች ከግል ሌቦች ጋር በመመሳጠር ከፍተኛ ሙስና እየፈጸሙ ናቸው" ሲል እየተካሄደ ያለውን ዘረፋ እንደሚያውቅ መስክሮአል። የርሱን ዲስኩር ተከትለው እራሳቸው ተጠያቂ ስለሆኑበት ሙስና ውግዘት ከጀመሩት አንዱ የሆነው የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትሩ ጁነዲን ሳዶ አሰራርን በማሻሻልና አቅም በመፍጠር ከፍተኛ ለውጥ ያመጣል የተባለው ቢ.ፒ.አር. ያለ አንዳች ስኬት አዳዲስ ካድሬዎችን ወደ ስልጣን በማምጣት ብቻ ማክተሙን አምኗል። በአቅም ድክመት ተገምግሞ ከኦሮሚያ ክልል ፕሬዘደንትነት የተነሳው የአሁኑ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ኩማ ደመቅሳም በበኩሉ ኪራይ ሰብሳቢነት አላሰራ ያለና የህዝብ አመኔታ ያሳጣ ችግር መሆኑን ይፋ አድርጓል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የሰው ልጆች መብት ተሟጋችና የኢትዮጵያ ህዝብ ታላቅ ወዳጅ የነበሩት አሜሪካዊው ኮንግረስ ማን የዶናልድ ፔይንን ህልፈተ ዜና አስመልክቶ የግንቦት 7 ንቅናቄ የሃዘን መግለጫ አወጣ

የኒውጀርሲን ግዛት በመወከል የመጀመሪያው ጥቁር አሜሪካዊ የተወካዮች ምክር ቤት ተመራጭ የሆኑት ዶናልድ ፔይን ከትናትና በስቲያ ማክሰኞ የካቲት 27 2004 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት መለየታቸውን ምክንያት በማድረግ ንቅናቄያችን ግንቦት 7 ባወጣው የሃዘን መግለጫ፤ በአንጀት ካንሰር ምክንያት ለሞት በመዳረጋቸው የተሰማውን ጥልቅ ሃዘን ሲገልጽ አሜሪካውያን ታላቅ አርበኛቸውን፤እኛ ኢትዮጵያውያን ደግሞ ታላቅ ወዳጃችንን አጥተና ” ብሏል

ዶናልድ ፔይን ለታፈነው የኢትዮጵያ ህዘብ ድምጽ በመሆን፣ የሰው ልጆች መብት ሁሉ እንዲከበር ፤ ዲሞክራሲና የህግ የበላይነት በአፍሪካና በመላው ዓለም እንዲሰፍን ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የሚታገሉ ሰው ነበሩ ያለው የንቅናቄው መግለጫ፤ ከህመማቸው ተፈውሰው የመረጣቸውን ህዝብ በቀጣይነት ለማገልገልና ለመላው የሰው ልጆች ነጻነት ያላቸውን ተቆርቋሪነት እስከመጨረሻው ለመግፋት የነበራቸው ምኞትና ጉጉት ከፍተኛ እንደነበረ ገልጾአል።

ዶናል ፔይን በአሜሪካን የተወካዮች ምክርቤት ውስጥ ኤች አር 2003 - የተባለው “የኢትኦጵያ የዲሞክራሲና የሰብዓዊ መብቶች ረቂቅ አዋጅ ቁጥር 2007” ህግ ሆኖ እንዲጸድቅ በተጫወቱት ታላቅ ሚናና በሰጡት አመራር በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያ አመሪካዊያንን ክብርና አድናቆት የተቸሩ ናቸው ያለው የግንቦት 7 ሃዘን መግለጫ፤ በርሳቸው ሞት ምክንያት መሪር ሃዘን ላይ ከወደቁ ቤተሰቦቻቸው ጋር በሃሳብና በጸሎት አብረን ነን በማለት በመላው የንቅናቄው አባላት ሥም ለመላው ቤሰተቦቻቸው፣ለጓደኞቻቸው፣ ለአጋሮቻቸውና ለስራ ባልደረቦቻቸው ልባዊ መጽናናትን እንደሚመኝ አስታውቆአል።

ዶናልድ ፔይን ለ27 አመታት ያህል የኮንግረስ አባል ሆነው በሰሩበት ወቅት የአሜሪካ የውጪ ግንኙነት ኮሚቴንና የአፍሪካ ጉዳይ ኮሚቴን ጨምሮ በተለያዩ የሥራ ሃላፊነት ላይ ቅን አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ ታላቅ የህዝብ አገልጋይ በመሆን የሚታወሱ ናቸው።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## "ጊዜው የትብብር ነው!!!" – የጥምረት-ኦነግ ስብሰባዎች መልዕክት

ጥምረት ለነፃነት፣ ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያ (ጥምረት) በጄኔራል ከማል ገልቹ ከሚመራው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) ጋር በመሆን በአምስት አገሮች ውስጥ በሚገኙ 11 ከተሞች ህዝባዊ ስብሰባዎችን እያካሄደ ነው። በዩናትድ ስቴትስ አሜሪካ በ7 ከተሞች፤ በካናዳ በሁለት ከተሞች፤ በጀርመንና በኖርዌይ ደግሞ በአንዳንድ ከተሞች ህዝባዊ ስብሰባዎች ይደረጋሉ። እስካሁን ስድስት ስብሰባዎች ተደርገዋል፤ አምስት ይቀራሉ።

እስካሁን በተደረጉት ህዝባዊ ስብሰባዎች በጣም አበረታች ምልክቶች ታይተዋል።

- በጄኔራል ከማል ገልቹ የሚመራው ኦነግ በኢትዮጵያ ጥላ ስር ሆኖ ከሌሎች የዲሞክራሲ ኃይሎች ጋር ተባብሮ ለመሥራት ያስተላለፈው ውሳኔ ያስደሰታቸው ወገኖች ደስታ ለመግለጽና ለትግሉም የበኩላቸውን ለማበርከት በብዛት ወደ ስብሰባ አዳራሾች ተመዋል፤
- ኦነግ የአቋም ለውጥ ማድረጉን ሰምተው የተጠራጠሩ በገዛ ራሳቸው ጆሮዎች ለመስማት ሲሉ መጥተዋል፤
- በኢትዮጵያ ፓለቲካ ተስፋ ቆርጠው የነበሩት በሰሙት ዜና ተስፋቸው አንሰራርቶ ተገኝተዋል፤
- ግንቦት 7 በሚያደርጋቸው ጥረቶች የተበረታቱ ሆኖም ያልተመለሱ ጥያቄዎች የነበሯቸው ወገኞችም ጥያቄዎቻቸውን ለማቅረብ ተገኝተዋል። ጥያቄዎቻቸውን አቅርበውን ምላሽ አግኝተዋል።

ይህ በእጅጉ ተስፋ ሰጭ ጅማሮ ነው። ለዓመታት ባልነበረ ሁኔታ አዳራሾች ተጣበው ታይተዋል። በሁሉም በላይ አስገራሚው ነገር ይህ አዎታዊ ለውጥ የታየው እስካሁን ስብሰባ በተደረገባቸው ስድስቱም ቦታዎች መሆኑ ክስተቱ ከአንድ ከተማ ወይም አገር ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገናኘ ያለመሆኑ ማረጋገጫ ነው። ይህ ክስተት በኢትዮጵያ ፓለቲካ ውስጥ አንዳች አዎታዊ ለውጥ እየመጣ እንደሆነ ያመለክታል።

የመለስ ዜናዊ ዘረኛ ቡድን ኢትዮጵያዊያንን በዘር፣ በሃይማኖት፣ በሙያ፣ በሃብት እየከፋፈለ፤ አንዱን ከሌላው እያጣላ አገዛዙን በማጠንከር ላይ በሚገኝበት በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያን እየተሰባሰቡ መምጣቸው ነፃነት ናፋቂውን ህዝብ ያስደሰተ ጉዳይ ነው።

"ድር ቢያብር አንበሳ ያስር" እንዲሉ እኛ ኢትዮጵያዊያን በጋራ ከቆምን ዘረኛውና አምባገነኑን መለስ ዜናዊና ቡድኑን ከሥልጣን ማስወገድ ብቻ ሳይሆን በምትኩ ፍትህ የሰፈነባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መገንባት እንችላለን። በየስብሰባ አዳራሾቹም የተሰማው ይህ የተስፋ ማንሰራራት ስሜት የወለደው ልበ ሙሉነት ይህ ነበር።

የኢትዮጵያ ህዝብ ኅብረትን ሲናፍቅ መቆየቱ የጥምረትና የኦነግ የጋራ ስብሰባዎች ያረጋገጡልን ሃቅ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ በዓላማ በጣም የተለያዩ በሚመስሉ ድርጅቶች መካከል ኅብረት መፈጠሩ ኢትዮጵያዊያንን ማስደሰቱ ከስብሰባዎቹ የተገኘ አንድ አቢይ ተጨባጭ መልዕክት ነው። ድርጅቶች በቶሎ ኅብረትን ፈጥረው ኢትዮጵያ ውስጥ የሚያደርጉትን ትግል በማስተባበር የመለስን ዘረኛና አምባነገን ሥርዓትን ለመገርሰስ የሚደረገውን ትግል እንዲያጧጥፉ የኢትዮጵያ ህዝብ እየወተወተ መሆኑ ከስብሰባዎቹ የተገኘ ሌላ አቢይ ነጥብ ነው።

እነዚህ ስብሰባዎች "ጊዜው በመርህ ላይ የተመሠረተ ትብብር መፍጠሪያ ነውና፤ ራሳችሁን መርምራችሁ ለትብብር ዝግጁ ሁኑ፤ ተግራዊ እንቅስቃሴዓችሁንም አፋጥኑ" የሚል ጠንካራና ግልጽ ጥሪ ለሁሉም ድርጅቶች አስተላልፏል። ሁሉም የኦነግ አካላትና ሌሎች ድርጅቶች ይህ ጥሪ ይቀበላሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የተስፋ ጭላንጭል እያሳየ ያለው የትብብር መንፈስ እንዲጎለበት የበኩሉን የሚቻለውን ሁሉ ብርቱ ጥረት ያደርጋል። ግንቦት 7 የትብብር አድማሳችንን ማስፋት አለብን ብሎ ያምናል። የምንፈጥራቸው ትብብሮችም ዘላቂና አዝላቂ እንዲሆኑ ከጅምሩ ጀምሮ በጥንቃቄ ሊገነቡ ይገባል ብሎ ያምናል፤ ለዚህም የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማበርከት ዝግጁ መሆኑ በድጋሚ ያረጋግጣል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## ወያኔ የጋምቤላን አውሮፕላን ማረፊያ በብረት ለበስና በታንክ እንዲጠበቅ ሲያደርግ በመላ ክልሉ ሰፊ ቁጥር ያለው ወታደር አሰማራ

ከአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በክልሉ በካራቱሪ እርሻ ጥበቃ ስራ ላይ ተሰማርተው የነበሩ ሶስት ሰዎች ሲገደሉ አንዱ ቆስሏል። በክልሉ ያለው ውጥረት መባባስ ያሳሰበው አምባገነኑ መንግስት በከፍተኛው ካድሬ ም/ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር በሀይለማሪያም ደሳለኝ የሚመራ ቡድን ወደ ጋምቤላ ልኳል።

በጋምቤላ የኢኮኖሚ ችግር፣ሙስና፣ የመሬት ነጠቃ፣ አስገድዶ ከቀዬ ማፈናቀል በግፍ ከተፈጸመው ጭፍጨፋ ጋር በመዳመር ውጥረቱን አባብሰውታል። በወያኔ እየተካሄደ ያለውን የክልሉን መሬት ለውጪ ባለሀብቶች የመቸብቸብ እንቅስቃሴ ተቃውሞ እንደቀጠለ ነው።

በጋምቤላ ዜጎችን ከቀያቸው እያፈናቀሉ መሬትን ለባእዳን የመሸጥ ዘመቻ ተቃውሞ ከቀሰቀሰ ወዲህ በተለይ ላለፉት 2 ና ሶስት ወራት ማንነታቸው በግልጽ ያልታወቁ ታጣቂዎች በወያኔ ቅጥረኛ አገልጋዮችና ካራቱሪ በተባለው የህንድ ካምፓኒ ጥበቃ ሰራተኞች ላይ እርምጃ መውሰድ በመጀመራቸው በክልሉ ውጥረት ሰፍኖ ይገኛል ተብሎአል። ይህንንም ተከትሎ በክልሉ በስፋት የተሰማራው ጦር አውጫጪኝ ያካሄደ ቢሆንም አንዳች ውጤት ሳይገኝበት ቀርቷል።ለሽፍቶቹ ምግብ እንዳትሰጧቸው፣መጠለያም እንዲሁ ለሚለው ትእዛዙ ጦሩ ያገኘው መልስ ጫካው ሙሉ ምግብ ነው፣ ደኑም መጠለያቸው ነው የሚል ነበር።

በተከታታይ ከተፈጠረው ከክልሉ ዓመጽ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የጋምቤላ አውሮፕላን ማረፍያ በብረት ለበስና በታንክ እየተጠበቀ ነው።ከፍተኛ ቁጥር ያለው እግረኛ ጦርም መላ ክልሉን አጥለቅልቆታል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ባሳለፍነው ሳምንት የመለስ ዜናዊ ታማኝ አገልጋይ በመሆን ለይስሙላ ለምክትል ጠቅላይ ምንስተሪነትና ለውጪ ጉዳይ ሚንስትርነት የበቃው ሀይለማሪያም ደሳለኝ ከጋምቤላው ፕሬዘደንት ኦሞት ኦባንግ ጋር ወደ ደቡብ ሱዳን ማምራታቸዉን ለማወቅ ተችሎአል። የጉዟቸው ዓላማም የክልሉን ጸጥታ በማስመልከት ከደቡብ ሱዳን ባለስልጣናት ጋር ለመነጋገር ነበር ተብሎአል። ሃይለማሪያም ደሳለኝ በጉብኙቱ ወቅት ከሁለት ወራት በፊት የኑዌርና የሙርሲ አባላት ተጋጭተው ከሁለት ሺህ የማያንሱ ሰዎች መሞታቸውን አንስቶ እንደነበርና በጋምቤላ ክልል እየታየ ያለው የጸጥታ ችግርን በመደጋገፍ መቆጣጠር ካልተቻለ የደቡብ ሱዳንን አኙዋክ ምድር አልፎ ወደ ጂቡቲና ኬንያ የሚዘረጋውን የነዳጅ መስመር ግንባታ ሊያስተጓጉለው እንደሚችል ማስጠንቀቁን ተያይዞ የደረሰን ዜና ገለጸ።

ኦሞት ኦባንግም በበኩሉ የክልሉ ተወላጅ የሆኑ የመንደሩን ሰዎች አፈላልጎ ጥቃቱን የሚሰነዝሩ ሰዎች እነማን እንደሆኑ ለማውጣጣት ሙከራ አድርጎ እንደነበርና እንዳልተሳካለት ሆኖም የአካባቢው ሰዎች ከአሁን ቦኋላ የሚያገኙትን መረጃ በኢንቨስትመንት ስም በጁባ ለሚንቀሳቀሱ የትግራይ ተወላጅ የወያኔ ካድሬዎች እንዲያቀብሉ አስተዋውቋቸዋል ተብሎአል። ጥቆማውን ለማካሄድ ፍቃደኛ ለሚሆኑ ሰዎች ለያንዳንዳቸው በወር አንድ ሺህ ዶላር ደሞዝ እንደሚከፈላቸው በመንገር ተማጽኗቸዋል እንደ ለአዲስቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ መረጃ ።

ከዚያው ከጋምቤላ ክልል ዜና ሳንወጣ ኢታንግ ውስጥ ባሉ ትምህረት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ከአራት ወራት በላይ ደሞዝ ሳይከፈላቸው በመቆየቱ ምክንያት የሥራ ማቆም አድማ እንዳደረጉ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ዘገባ አመልክቶአል።

በሰሜን የአገራችን ክፍል በጎንደር ያሉ መምህራን በቅርቡ የስራ ማቆም አድማ አድርገው እንደነበርና የአማራ ክልል መምህራን ማህበር ባቀረበው የሙብት ጥያቄ የተደናገጠው ወያኔ በመምህራን ዘንድ ውክልና የሌለውን የማህበር ሊቀመንበር በማስመረጥ ተግባር ላይ እንደከረመ የኢትዮጵያ ሳታላይት ተለቪዥን ከትናት በስቲያ ዜናው መዘገቡ ይታወሳል።

---

## የሰው ልጆች ሙብት ተሟጋችና የኢትዮጵያ ህዝብ ታላቅ ወዳጅ የነበሩት . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ድህረ ምርጫ 97 የዘረኛው መለስ ዜናዊ በወሰደው እርምጃ በቃሊቲ እስር ቤት ታጉረው የነበሩ የቅንጅት መሪዎችና ደጋፊዎች ተፈተውና የተጭበረበረው የምርጫ ድምጽ ተመልሶ አገራችን ወደ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እንድታመራ መለስ ዜናዊን ለማሳመን ወደ አዲስ አበባ ከመመላለሳቸውም በላይ የኢጋዚ ጦር በመለስ ቀጥተኛ ትዕዛዝ በንጹሃን ዜጎቻችን ላይ የፈጸመው ጭፍጨፋ እንዲጣራ ከፍተኛ ግፊት ያደረጉ የፍትህ ተቆርቋሪ ሰው ነበሩ።

## የእሳት እራት
## ትውስታየ በውጭ ጉዳይ ሚንስቴር

(ክፍል 3 ካለፈው ሳምንት የቀጠለ)

የቢሮየ ተጋሪ ደመወዙ ተጨምሮበት በወር ከ43 ሺህ ብር በላይ ገቢ ያገኛል። እኔ በወር የተጣራ 520 የኢትዮጵያ ብር ሲደርሰኝ እርሱ ያን ያክል ማግኘቱ በዜጎች መሃከል እየተፈጠረ ያለውን የሃብት ክፍፍል ልዩነት ለማሳየት ጥሩ ምሳሌ ነው። እርሱም የመጀመሪያ ዲግሪ አለው። እኔም ከአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የመጀመሪያ ዲግሪ አለኝ። ታዲያ ይሄ ሁሉ ልዩነት እንዴት ተፈጠረ ? እንደሰው ለፍቶ ጥሮ ግሮ በላቡ በወዙ አግኝቶ ልዩነቱን ፈጥሮ ቢሆን መልካም ነበር። ነግሩ ግን እንዲያ አይደለም። ዝርፊያ ነው። አገሪቷ የእነርሱ ስለማትመስላቸው የመንግስትን ስልጣን ተገን አድርገው ኮንትራባንድ ይነግዳሉ። መሬት ይነጥቃሉ ይሸጣሉ። ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ማንኛውንም ወንጀል የተባለ ነገር ሁሉ ይፈጽማሉ። በአጠቃላይ አገሪቷን ባለው መንገድ ሁሉ በመቀራመት ተግባር ላይ ተጠምደዋል። የአገሪቷን መሬት እንደልባቸው ለመሸጥና ለመለወጥ ህወሃቶች መብቱ አላቸው እኔ ያ መብት እንዳይኖረኝ በህግ ደህና ተደርጌ ታስሬአለሁ። እነርሱ የዜጎችን መሬት ነጥቀው ይሸጣሉ ይለውጣሉ። እኔ ግን ወላጆቼ ያወረሱኝን መሬት እንኳ እንዳልሸጥ እንዳልለውጥ ህግ ተሰርቶልኛል። የህወሃት ዓባል የሆነ ሁሉንም ነው። ለእነርሱ ወሰንና ገደብ የለም እነርሱ ከሁሉ በላይ ናቸው።

መጥኔ ለህወሃቶች !!! መጥኔ ለእነርሱ !!!ብለን እንቀጥል።
እኔ የህወትን በጎ ነገር የማውቀው የለም። የዚህ ድርጅት አባል መሆን አሳፋሪ ነው። ህወሃቶች ግን እፍረትን አያውቁም። እንዲያውም በነውራቸው ኮርተው በትግራይ 100% በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች ደግሞ በ99.6% ተመርጠናል በማለት አገሪቷን በግምት እየገዟት ይገኛሉ። ምን ያድርጉ ሰው የሌለበት ባዶ ቤት አገኙ ያንንም ቤት ጠያቂ ጠፋ እነርሱም በዚያ ጌቶች ሆኑ።

አሁንም ወደ ቢሮየ ተጋሪ ሰው እንመለስ። ከዚህ ሰው ጋር ብዙም ማውራት አልወድም። ክፉ ትእቢተኛ ነው። ሃይማኖቱን የማያውቅ ወይም ደግሞ የዓለሙን ነገር በደንብ የማይገነዘብ ዞንቢ ነው። ለሰው ልጆች ክብር የሚባል ነገር በውስጡ አልተፈጠረም። እኔን የሚያክል ልጅ ወልዶ ሲያበቃ ከአንደበቱ የሚወጣው ነውር አስደንጋጭ ነው። በሽምግልናው ወቅት እንኳ ራሱን መግራት ያልቻለ ግለሰብ ነው። እርሱን ብቻ የሚያውቅ ሰው በትግሬዎች ላይ ብርቱ ጥላቻን ያሳድራል። እርሱን የመሰሉ ብዙ የትግሬዎችን መልክ የሚያጠፉ ከንቱ ግለሰቦች ሞልተዋል። እኔ ተወልጄ በኖርኩበት አካባቢ ትግሬዎች የሚገለጹት በታማኝነታቸው፤ በታታሪነታቸው፤ በየዋህነታቸው እና በግልፍተኝነታቸው እንጂ በጨካኝነት፤ በስግብግብነት፤ በሌብነት እና ጥላቻን በመዝራት አልነበረም። አሁን የቢሮየን ተጋሪ የመሰሉ ህወቶች ያስተዋወቁን ትግሬዎች እኛ ድሮ የምናውቃቸውን አይደለም። ከህወሃቶች በፊት እኛ የምናውቃቸው ጥሩ ትግሬዎች አሁን የት እንዳሉም አላውቅም። ምን አልባት እነዚህ ተኩላዎች የዋሃን ርግቦችን በልተው ጨርሷቸው እንደሆነም አላውቅም።

ይህ የቢሮየ ተጋሪ አንዳንዴ ያለ ሥራ ወደ ውጭ አገር መሄድ ፈልጎ ከተከለከለ ስዩምን ደደብ አህያ እያለ ይሳደባል። መለስን ደግሞ ጀግና እያለ ያሞካሻል። እንደፈለገ ቢል እኔ ግን ምንም አስተያየት አልሰጥም። እኔ ዝም የምለው እርሱ ወሬ ከእኔ ቀድቶ ለሌሎች ያስተላልፋል ብየ ሳይሆን ተፈጥሮየ ስለሆነ ነው። የሰውን ስም እያነሳሁ በእንዲህ ዓይነቱ ነውር ነገር ውስጥ መሳተፍ አይመቸኝም።

እንዲሁ ዝም እንዳልኩ አራት ዓመቱ ደረሰና ወደ ውጭ አገር የመመደብ ምኞቴ እውነት ወደ መሆን ተቃረበ። የት አገር ይመድቡኝ ይሆን እያልኩ ማሰብን ተያያዝኩት። ኤምባሲዎቻችን ውስጥ ያሉ ክፍት ቦታዎችን አጠናሁ። አንዳንድ አገሮችንም መርጬ ለኑሮ መልካም ይሆኑ እንደሆነ አጠናሁ። ነገሮች ሁሉ መልካም መሰሉኝ። በነገራችን ላይ አንድ የውጭ ጉዳይ ሚንስትር ሠራተኛ ወደ ውጭ አገር ያሉ ኤምባሲዎች ከተመደበ ከሲኦል ወደ ገነት እንደተዛወረ ይቆጠራል። በዘመድ አዝማድ መካከልም ፍጹም ደስታና እፎይታ ይሆናል። ድሮ ድሮ ወደ ውጭ አገር መላክ እንደ ግዞት ይቆጠር ነበር ሲባል ሰምቼ ነበር። የህወሃት እድገት ያመጣው አንዱ ፈተና አንድ ሰው ከቀየው ከመንደሩ ተነቅሎ ሲሄድ ፍጹም ደስታንና እፎይታን የማግኘቱ ሚስጢር ነው።

እኔም ወደ ውጭ መሄጃየን ግዜ እያሰብኩ ለቤተሰቦቼ አይዟችሁ ያዘመመ መኖሪያችን የሚታደሰብት ግዜው ደርሷል እያልኩ አጽናናቸው ጀመር።

ወላጆቼም በተስፋ ተሞልተውና ደስ እያላቸው ይመርቁኝ ጀመር። ሊወድቅ ያዘመመን ቤት ስጠግንላቸው እየታየኝ እኔም ውስጤን ደስ ሲለው ተሰማኝና መስሪያ ቤቴንም ወደደኩት። ይሄን እድል ለሰጠችኝ አገር ታምኜ ማገልገል እንዳለብኝም ራሴ ለራሴ ቃል ገባሁ።

ሙዝ በዳቦ ከመብላት ልላቀቅ መሆኔንም እያሰብኩ ዘና አልኩ። ከምደባየ ስመለስም እንደ ቢሮየ ተጋሪ በወር 42 ሺህ ብር ማከራየት የምችለው ዓይነት ቤት ባይኖረኝም ከግለሰብ ኪራይ ቤት ወጥቼ የራሴ ማደሪያ ሊኖረኝ እንደሚችል አለምኩና ደስ አለኝ። በዚያች አገር ከዚህ በላይ ምን እንዳስብ ይጠበቅብኝ ይሆን? ሌላ ነገር ማሰብ ወንጀል የሆነበት አገር ውስጥ ምን ላስብ እችላለሁ ?

እንዲህ ምድባየን በተስፋ እየጠበኩ ባለበት ወቅት የ1997 ዓ.ም ምርጫ ተቃረበ ቀስ በቀስም ቅንጅት የተባለ ድርጅት መጣ። ሁሉም በያለበት ሁኖ ክርክሩን ተከታትሏል። ግሩም ድንቅ ክርክርና ውድድር ነበር። የኢሕአዴግ ቱባ ቱባ ባለስልጣኖች በቴሌቭዥን መስኮት ብቅ እያሉ ክርክር ሳይሆን ስድብ መሰል ነገር ያዙ። የቅንጅት ተከራካሪዎች በትምህርት ደረጃቸው የላቁ በመሆናቸው ለክርክሩ አንብበው ተዘጋጅተውበትና የሚናገሩትን አውቀው ሲመጡ ስዩምን ጨምሮ የኢሕአዴግ ዋና ዋና የተባሉ ሰዎች ትእቢታቸውንንና ባዶነታቸውን ብቻ ይዘው መጡና አይቼ በትካዜ ተዋጥኩ። ከዚያም "ኢንተርሃሞይ" የተባለ ባእድ ቃል በመጨመር የክርክሩን ድባብ አጨለሙት። የውጭ ጉዳይ ሠራተኛ መሆኔን የሚያውቁ "ለመሆኑ እነዚህ ናቸው እንዴ አገር የሚመሩ" እያሉ ለሚጠይቁኝ መልስ መስጠት ተሳነኝና ዝም ማለትን ምርጫየ አደረኩት።

ለሚነሳው ጥያቄ ሁሉ መልሳቸው የደርግና የትምክህተኛ ጥያቄ እያሉ በመሳደብ ጥሩ ደጋፊዎቻቸውን ሁሉ አሳፈሩ። እኔም አፈረኩባቸው። እነርሱ ግን እፈረት አያወቁም። እንዲያውም በነውራቸው እርስ በርሳቸው ሲሞጋገሱ ሰምቼ በጣም ተገረምኩ። ነውራቸው ክብራቸው የሆኑ ዜጎች በአገዛ አገሬ ላይ መሰልጠናቸውን ሳይ አዘንኩ።

የቢሮየ ተካፋይም "አይ በረከት ወንድ ነው። ልክ ልካቸውን ነገራቸው እኮ። ይሄ ትምክህተኛ ሁሉ ስልጣን እንዲሁ ሊወስድ ይፈልጋል እኮ እያለ ይፎክራል። ደግሞ አያፍሩም መሬት ይሸጥ ይላሉ እነዚህ የኤምፔሪያልዝም ርዝራዦች" እያለ ቅንጅቶችን ይሳደባል። እርሱ ግን ሁለተኛ ቤት ሊሰራበት መሬት ለመግዛት ላይ ታች ይላል። ህወሃቶች እንዲህ ናቸው። ሌላውን ይከለክላሉ እነርሱ ግን በዚያ ሥፍራ ዋነኛ ተዋኒያን ይሆናሉ። ብዙዎቹ ይሄ ነውር መሆኑን የሚረዳ ሂሊና የላቸውም። አገርንም የሚያፈርስ ተግባር መሆኑን አይረዱትም። ወይም ለመረዳት አይፈልጉም።

በተቻለኝ ሁሉ ከዚህ ሠው ጋር ምንም ዓይነት አገራዊ ጉዳይ ላለማውራት እጠነቀቃለሁ። የእነርሱ አገር እና የእኔ አገር የተለያየች ሁናለች። እኔ ስለእነርሱ አገር ማውራት ፍላጎት የለኝም። ስለዚህ ዝም ማለት የተሻለ አማራጭ ነው ብየ አምን ነበር።

አንድ ቀን ስለ ባድሜ ጉዳይ ተነሳና አፌን ከፈቼ አስተያየት ሰጠው። ወደ ጦርነቱ መግባቱ ትክክል ነው ብየ አላምንም አልኩ። ከተዋጋንና ያ ሁሉ ሰው ከሞተ በኋላ ደግሞ አልጀርስ ድረስ ሂዶ ይግባኝ የማይባልበት ስምምነት መፈራረም ትክክል ነው ብየ አላምንም ስል ጨመርኩ።

እንዴት? አመራሩ አምኖ ትክክል ነው ብሎ ያደረገውን አለማመን እኮ ችግር አለው። ይህ ማለት ደግሞ በአመራሩ ችሎታና ብቃት ላይ ጥራጣሬ አለህ ማለት ነው ሲል ደመደመው።

ከዚህ በኋላ ምን መነጋገር ይቻላል። ለማንኛውም ጉዳዩ ከሮ ሌላ ነገር እንዳያስከትል ስለሰጋሁ እንዲህ አልኩት ይሄ የመጠርጠር ያለመጠርጠር ጉዳይ ሳይሆን በነገሩ አጀማመርና አፈጻጸም ላይ ግልጽነት ስለሚጎለው እውቀት የለኝም ለማለት ነው ።

ይገርማል አለ።
እዚህ ውስጥ ምን የሚገርም ነገር አለው ስል ጠየኩት።
ብዙ የሚገርም ነገር ብሎ ዝም አለ። ከዚህ በኋላ አልተነጋገርንም።
ይህች እለትና ይህች ንግግር ተስፋየንና ምኞቴን ያመከነች መሆኗን የተገነዘብኩት ብዙም ሳልቆይ ነው።

የአዲስ አበባ ህዝብ በሙሉ ቅንጅትን በመምረጡ በህወሃት ፤የውጭ ጉድይ ሰራተኛ ደግሞ በስዩም መስፍን ጥርስ ውስጥ ገባ። ስዩምም ከሠራተኛ አስተዳደር የሠራተኞችን ስም ዝርዝር አስመጥቶ ከእነዚህ ውስጥ ባስቸኳይ 10% ይባረር ሲል መመሪያ ሰጠ። 10%ቱን ረሽኑ ቢልስ ማን ይከለክለው ነበር ?

በቃ አስር ፐርሰንቱን አባርሩ ብሎ ቀጭን ትእዛዝ አስተላለፈ። ከአራት መቶ ሃያ ሰራተኞች መካከል 42 ሰው መባረር አለበት። በተለይ አማራ፤ኦሮሞና ጉራጌ ትኩረት ተደረገበት። ከተባረሩት 42 ሠራተኞች መካከል አንድም ትግሬ አለመኖሩ ነገሩ በሌሎች በተለይም በአማራ በኦሮሞና በጉራጌ ብሄር አባላት ላይ ያነጣጠረ መሆኑ ታወቀ። የተባረሪውም ያልተባረረውም ሠራተኛ በትግሬዎች ላይ ቂም እንዲይዝ አላደረገም ማለት አይቻልም። የህወሃትም ምኞትና ፍላጎት ይሄው ነው። ትግሬዎችን ከሌላው ህዝብ ለይቶ የሥርዓቱ ተጠቃሚ አድርጎ ማሳየትና በሌላው ህዝብ እንዲጠሉ ማድረግ። በዚህ ረገድ ይሳካላቸው አይሳካላቸው ወደፊት የሚታይ ይሆናል። ጥላቻ ሥጋ ለብሶ ቁሞ እንዲሄድ ህወሃቶች ቀንና ማታ እየሰሩ ነው። ሥጋው ነፍስ የዘራ እለት ግን አገራችን ብዙ ሳታለቅስ አትቀርም። እግዜር እዚያ ደረጃ አያድርሰን ከማለት በቀር አሁን ምን ማድረግ እንዳለብን እንኳ አናውቅም። ለማንኛውም ትግሬዎች ሆይ ዝም አትበሉ። በእናንተና በሌሎች መካከል መለስ ዜናዊ የሚገነባውን የጠብ ግድግዳ ለማፍረስ መነሻ ግዜው አሁን ነው።

እኔ አማራም ኦሮሞም ነኝ። ኢሕዴግንም አምርሬ የምጠላ አልነበርኩም። እንዲህም በመሆኔ የመባረሩ ነገር እኔን ይመለከታል ብየ አላሰብኩም። እኔ ለመንግስት ታማኝ አገልጋይ መሆኔን ስለማውቅ መባረሩን እንደ እኔ ዝም ማለትን ልማድ ላላደረጉ ትቼ ጥቅሜን ብቻ ማሰብ ያዝኩ።

አስር ፐርሰንቱን መርጠው የሚያባርሩ ግለሰቦች በሚስጥር ተመርጠው በስዩም መስፍን ተሰየሙ። ኋላ እንደታወቀው በመስሪያ ቤቱ ውስጥ የነበሩት ህወሃቶች በቅንጅት ነውጥ ተደናግጠው ስለነበረ ለውጥ ፈላጊ ሃይሉን በሙሉ የ"ትግሬ" ጠላት ነው ብለው ፈርጀው ለማባረር ቆርጠው ተነሱ። በወቅቱ ለውጥ ፈላጊውን መርጠው ለማባረር በትጋት የሰሩና "ህወትን መቃወም ትግሬን መቃወም" ነው ብለው የሚያምኑ ናቸው የተባሉ ግለሰቦች ስም ዝርዝር የሚከተለው ነው።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ኢትዮጵያ በህግ የተገደበ ስልጣንና፤ በሰብዓዊ መብት አያያዝ ከ9 የሳሃራ አፍሪካ አገሮች የመጨረሻው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደምትገኝ አንድ ገለልተኛ የሆነ አለም አቀፍ ድርጅት ጥናት አጋለጠ

ጥናቱን ያካሄደው "ዓለም አቀፍ የፍትህ ተቋም ፕሮግራም፣ የህግ የበላይነት ጠቋሚ ጥናት በ እንግሊዘኛ World Justice Program 2011 Rule of Law Index ይፋ እንዳደረገው ኢትዮጵያ ከሰሃራ በታች ከሚገኙ 9 አገሮች የመንግስት ሥልጣን በመጠቀም በህግ አውጪውና በህግ ተርጓሚው ላይ ተጽዕኖ በመፍጠር፣ የዳኝነት ሥርዓት ውስጥ ጣልቃ በመግባት፤ ነጻ የኦዲት ስርዓት እንዳይኖር በማድረግ፣ የመንግስት ባለስልጣናት ለህግ ተገዢ ባለመሆንና መንግሥታዊ ስልጣንን በነጻና ፍትሀዊ ምርጫ ባለማስተላለፍ ከመጨረሻው ዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆኗን አመለከቶአል።

ከሳሃራ በታች የሚገኙ አገሮችን ጨምሮ ጥናቱ ከተካሄድባቸው 66 አገሮች 60ኛ ደረጃ ላይ መሆኗ የተገለጸው አገራችን ስልጣን ላይ ያለው የወያኔ አገዛዝ ከግልጽነት እጅግ የራቀ መሆኑ ተጠቅሶአል።

ጥናቱ በሰብዓዊ መብት አያያዝ ረገድ የመሰብሰብና ሃሳብን በነጻ የመግለጽ ነጻነትን፣ በሃይል የሚደረጉ የመብት ጥሰቶችንና ህገወጥ እስርን ከግምት አስገብቷል። ከዚህ አኳያ በጥናቱ ከተካተቱ ሀገራት መካከል ሶስቱ ብቻ ከገደብ የለሽ የስልጣን ቁጥጥር ነጻ ሆነዋል። የኢትዮጵያ መንግስት ግልጽነት ከጎደላቸው ተርታ የተመደበ ሲሆን ህጎቹም ለህዝቡ በቀላሉ የማይገቡ፣ የግልጽነት ችግር ያለባቸውና ተደጋጋሚነት የሌላቸው ድንጋጌዎችም የሚታዩባቸው ተብለዋል። በተጨማሪም ህጋዊ መብትን ለመጠየቅ የማያመቹና ለተሳትፎ ዋስትና የሌላቸው ተብለው ተፈርጀዋል።

ህግ ሲረቀቅና ሲጸድቅ ተሳትፎ ከማይደረግባቸውና የፍርድ ቤቶችም የስራ አፈጻጸም ደካማ ከሆኑባቸው ሀገራት ውስጥ የተጠቀሰችው ኢትዮጵያ ሙስናም እንደ ዋነኛ የሀገሪቱ ችግር ተነስቷል። በዚህ ረገድም 62ኛ ደረጃ ላይ ተሰልፋለች። ጥናቱ ከአዲስ አበባ፣ ከድሬደዋና ከመቀሌ በድንገት ለናሙና በተመረጡ 1000 ሰዎችና በ19 ልዩ ልዩ የህግ ባለሙያዎች የተሞሉ መጠይቆችን መሰረት ያደረገ ነው። ሰነዱ በዓይነቱ በዓለም የመጀመሪያው እንደሆነም ተመልክቷል።

## ጥምረት ለነጻነት ፍትህና ለ እኩልነት ከኦርሞ ነጻነት ግንቦት ጋር

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

አርቲስት ታማኝ በየነ በተገኘባቸው ስብሰባዎች ሁሉ የወያኔን ደባና ተንኮል የሚያጋልጥ በቪዲዮ የተደገፈ መረጃ በማቅረብ የበርካቶችን ትኩረት እንደሳበ ከየስብሰባ አዳራሾቹ የደረሱን ዘገባዎች አመልከተዋል።

እስካሁን በተደረጉት ስብሰባዎች ላይ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን የተሳተፉ ሲሆን በኦሮሞ ነጻነት ግንባር ውስጥ የተካሄደውን ተሃድሶ የሚደግፉም ሆነ የሚቃወሙ በየስብሰባ አዳራሾቹ በመገኘት ያላቸውን አስተያየትና ጥያቄ በማቅረብ ለውይይቶቹ ውበትንና ስኬትን ሰጥተዋል ።

ጥምረትና ኦነግ በጋራ የሚያካሂዱት ስብሰባ በሚቀጥለው ቅዳሜ ማርች 10 በኦስሎ ኖርዌይ፤ እሁድ ማርች 11 በቶሮንቶ ካናዳና የወዲያኛው ሳምንት ማርች 17 በፍራንክፈርት ጀርመን ከተካሄደ በኋላ እንደፈረንጆች አቆጣጠር ማርች 24 ቅዳሜ በአሜሪካን አገር በሲያትልና በሚኒሶታ ከተሞች በሚደረጉ ህዝባዊ ስብሰባዎች ይጠናቀቃል።

## በኖርዌይ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ታላቅ የተቃውሞ

. . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ችግራችን ከግንዘቤ ይግባልን! ጉዳያችን እንደገና ይታይልን! የመኖሪያ ፈቃድም ይሰጠን ያሉት ተቃዋሚ ሰልፈኞች እኛም ወደ ሀገራችን ብንመለስ መጨረሻችን እስርና ሞት ነው በማለት በአጽንኦት ገልጸዋል። የኖርዌይ መንግስት ከመለስ ዜናዊ ጋር ያደረገው ይህ የመኖሪያ ፈቃድ የሌላቸውን ኢትዮጵያውያን የመመለስ ስምምነት ትክክል አይደለም ሲሉም ተቃውሟቸውን ደጋግመው ገልጸዋል።

ኖርዌይ የሰው ልጆችን መብት ከሚያከብሩ ሀገሮች አንዷ ሆና እያለ እንዴት እንዲህ አይነት ስምምነት እንደመለስ ዜናዊ ካለ ዘረኛ አምባገነን መሪ ጋር ትፈጽማለች በማለት የሚጠይቁት ተቃዋሞዎች በብዛት እዚሁ ኖርዌይ የተወለዱና ያደጉ ከ400 በላይ ህጻናት አብረውን አሉና የነሱስ ተስፋ እንዴት በዚህ ስምምነት ይወሰናል በማለት ለሚመለከተው ክፍል ጥያቄያቸውን አሰምተዋል።

በሰልፉ ላይ የተለያዩ ድርጅቶችን የሚወክሉ ግለሰቦች ንግግር ያደረጉ ሲሆን በተለይ ኑኣስ (NOAS) በመባል የሚታወቀው በኖርዌ የስደተኞች ተንከባካቢ ድርጅት ተወካይ በሀገራቸው በኖርዌይ እና በኢትዮጵያ መካከል የተደረገውን ይህን ስምምነት ችግር ያለበት እና ወቅቱን ያልጠበቀ እንደሆነ በመግለጽ ያወዝሁት ሲሆን ዘረኝነትን ከሚቃወመው ድርጅት (Anti-Raciest) የመጡት ደግሞ በኖርዌይ የስደተኞችን ጉዳይ የሚመለከተው መስሪያ ቤት (UDI) የስደተኞችን ጉዳይ በጥልቀት ከማየት ይልቅ ዉሳኔዎችን ኮፒ ፔስት (copy paste) በማድረግ አሰራር ተጠምዷል በማለት የድርጅቱን አሰራር ነቅፈዋል። በስምምነቱ መሰረት መጋቢት 6 2004 ዓ/ም (15 March, 2012) ኢትዮጵያዊያኑን አስገድዶ ለመመለስ የተቀመጠ የመጨረሻ ቀን እንደሆነ አስታውሰው ይህ ቀን የትግላችን መጀመሪያ እንጅ መጨረሻም አይሆንም በማለት ተቃዋሚ ሰልፈኛውን አበረታተዋል ከጠቃውሞ ሰልፉም ሞቅ ያለ ድጋፍን አግኝተዋል።

በመጨረሻም የተለያዩ መፈክሮችን ሲያሰማ የዋለው ሰላማዊ ሰልፍ አዘጋጆች የፊታችን March 12, 2012 ጠንካራና ዓለማቀፋዊ የተቃውሞ ሰልፍ እንደሚደረግ ማስታወቂያ ነግረው የሰልፉ ፍጻሜ ሆኗል።

በኖርዌ የሚገኙ መኖሪያ ፈቃድ የሌላቸውን ኢትዮጵያዊያን በፈቃድ ካልሆነም በግዳጅ ለመመለስ የኖርዌ መንግስት ከዘረኛው መለስ ዜናዊ ጋር ሐሙስ ጥር 17 2004 ዓ/ም (26 January, 2012) ስምምነት መፈራረሙ ይታወሳል።

## የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ተቋማትና ዘርፎች በሙስና ተተብትበዋል፣ .

. . (ከገፅ 1 የዞረ)

እነኚህንና ሌሎችንም ችግሮች ያነሳው ሪፖርተር የኢኮኖሚ ስኬት ዓላማና ፍላጎት በጽሁፍ ስላልሰፈሩ አይደለም በሁሉም መስክ ውድቀት የመጣው ይልቁንም ዋነኛ ችግሮቹ ሙስናና አቅም ማነስ ናቸው ሲል አብራርቷል። የወያኔ መንግስት ባለሙያዎችን ከየመስሪያ ቤቱ የድርጅቱ አባል ካልሆናችሁ እያለ በማባረር በድኩማን ካድሬዎች መተካቱ የውድቀቱ አንድ ምክንያት ነው የሚሉት አስተያየት ሰጪዎች ሀገሪቱን እየዘረፉ ያሉት የመንግስትና የግል ሌቦች ሁሉም የወያኔ አባላት መሆናቸውና ተጠያቂነት የሌለባቸው መሆኑ ሌላው ነው ብለዋል። እነኚሁ ባለሙያዎች ከ100 ሺህ ቶን በላይ ቡና የደረሰበት አለመታወቁን አስመልክቶ መለስ ዜናዊ በይፋ ባደረገው ንግግር "ሁላችንም ስለተነካካን ለአሁን እናልፈዋለን፣በቀጣይ ግን እኛ ስለማንኖርበት ሌባውን እንምረውም " ማለቱን በዋቢነት ይጠቅሳሉ።

ሪፖርተር በዚህ ዘገባው "ፍርድ ቤቶች ተደርምሰዋል፤ ይህ ዓይኑን ያፈጠጠ ሀቅ ነው፤ ሙስናና አሻጥር ፍትህን ሰለባ አድርገውታል" ካለ በኋላ ህዝብ ሙስና በዛ፣ ፍትህ ጠፋ፣ አቤት የሚባልበት የለም ብሎ እንደሚያማርር ጠቅሶ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ህዝብን ማገልገል አቁመው በህዝቡ እየተገለገሉበት ነው በማለት በህብረተሰቡ ውስጥ የሰፈነውን ብሶት ዘግቦአል።

## ትውስታየ በውጭ ጉዳይ ሚንስቴር

. . . (ከገፅ 3 የዞረ)

1ኛ. ወንድሙ አሳምነው
2ኛ. ሙሉጌታ ዘውዴ
3ኛ. ዋህደ በላይ
4ኛ. ካሳ ገ/ዮሃንስ
5ኛ. ኑረዲን ዓሊ
6ኛ. ቢነጋ ተወልደ

ሲሆኑ ፤ከቢነጋ ተወልደ በቀር ሌሎቹ በሙሉ የህወሃት አባላቶች ናቸው። ቢነጋ ተወለደ አባል ስለመሆኑ ጥርጣሬ አለ። የዚህ ታሪክ ባለቤት ቢነጋ ተወለደ እንዲህ ዓይነት ሰብቅ ውስጥ ይገባል ብሎ አያምንም። ብዙዎች የተባረሩት ግን ቢነጋን ከሌሎች ለይተው አያዩትም። እውነቱን ቢነጋ ራሱ ካለበት ሁኖ ሊነገረን ይችላል። ኑረዲን ዓሊ ከፖለቲካል ሳይንስ ትምህርት ክፍል በብዙ መከራ ተንጠልጥሎ የጨረሰ ነው። በውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ለመቀጠር ቢያንስ 3 ነጥብ ማግኘት ይጠበቅ ነበር። ህወሃቱ ኑረዲን ግን እንደምን ሆኖ እንደተቀጠረ ፈጣሪ ይወቀው። አብረውት የተማሩት የእርሱን ትምህርት የመቀበል አቅም ደካማነትን ሲናገሩ ስሰማ ህወሃትን በተጨማሪ ታዘብኩት።

እነዚህ በሚስጥር የተደራጁ ቡድኖች ሰራተኛው ሳያውቃቸው ውስጥ ለውስጥ የሌሎች ብሄር ተወካዮችን መርጠው እና ሴሎችን መሥርተው ጥናታቸውን ጀመሩ። ከዚያም ከሰራተኛው መካከልም ጓደኛሞችን እየከፈሉ ጓደኛህ ከመንግስት ፖሊስ በተቃራኒው ሁኖ መንግስትን የሚጎዳ ተግባር ፈጽሟል። አንተ ካሁን በኋላ እርሱን የምታድንበት መንገድ የለም። ስለአንተም የምናውቀው ነገር አለ ቢሆንም አንተ ብዙ ጉዳት አታደርስም ተሳስተህ ሊሆን ይችላል የሚል እምነት አለን። አሁን ስለ ጓደኛህ የምታውቀውን ንገረን እያሉ ያፋጥጡ ገቡ። ያ አራትና አምስት ዓመት እየራበው በውጭ ጉዳይ ቆይቶ የምደባው እድል እንዳታመልጠው የሚፈልግ ሁሉ ሂሊናውን ለኑሮው እየሸጠ ወንድምና እህቶቹን አሳልፎ ለመስጠት ልቡ ፈቀደና ለሚጠየቀው ሁሉ "አዎን እርሱ እንዲዚያ ብሏል። እርሷም እንዲያ ተናግራለች" እያሉ ምስክርነታቸውን ይሰጡ ጀመር። ይሄ እንግዲህ ህወሃት ብቻ ሳይሆን አገሪትን እየደረሰች ያለችበትን የሞራል ዝቅጠት የሚያሳያን አንዱ ክፍል ነው። አገርም ፈረሰ የሚባለው እንዲህ ሲሆን ነው። ለሚበላና ለሚጠጣ ብሎ ወንድም ወንድሙን እህት እህቷን አሳልፈው መስጠት የጀመሩ እለት አገርም አብራ መፍረስ ትጀምራለች። ከፉ መንግስትም የዜጎችን መልካም እሴቶች እያዋረደ መንገድ ሠራሁላችሁ እያለ ዜጎችን ያደርቃል። (ክፍል 4 ሳምንት ይቀጥላል)

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**መካከኛ ሞገድ፡-** በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ፡-** በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፤ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታሳውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ፡- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

### ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org